# አሳፋሪው የዩ.ኤስ.ኤይድ ጣልቃ ገብነት በኢትዮጵያ ሚዲያ

*ነሲቡ ታዬ ( ከኮልፌ )*

*ምርጫ 97-የ1997 ዓ.ም ምርጫ በታሪካችን ውስጥ ታላቅ የዴሞክራሲ ጅምር ተስፋ ሰጪ ሆኖ ተጀመረና በክህደትና በሸፍጥ በተሞሉ በውጭ ኃይሎች አይዞህ ባይነት ለበትረ መንግሥት ሥልጣን ተስፋ ባደረጉ ሕልመኞች ሁካታ፣ ግርግርና ሴራ በጐው ጅምር የታሪክ ጠባሳ እንዲጥል ሆኖ አለፈ፡፡ ያኔም ከተቃዋሚውና ከግሉ ፕሬስ ጀርባ የሚፈሰው ገንዘብ ከየት እንደሚገኝ ምንጬና ዓላማው ምን እንደሆነ በዲሞክራሲ ሥም እየተነገደና እየተቸረቸረ፣ በሰብአዊ መብት ጥበቃ ሥም የአዞ እንባ እየተነባና የፈጠራ ታሪክ እየተፃፈ፣ ዜና እየተሰራ፣ ሲያሻቸውም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እየተጠቀሰ ሕዝቡን በብርቱካናማው አብዮት ሥር ለማሰለፍ ብዙ ተደከመ፡፡ ተቃዋሚውንና የግሉን ፕሬስ አይዞህ እያሉ አጉል ተስፋ ሲቀልቡት የኢህአዴግ መንግሥት የአንድ ሳምንት እድሜ ብቻ የቀረው ነው በሚል የስሜት እብደት ተዘፍቀው በየድራፍቱና በየመሸታ ቤቱ ሲደልቁ ከረሙ፡፡ እውነቱ ከዚህ በእጅጉ የተለየ ከስሜታዊነት የራቀና በጭብጥ ላይ የተመረኮዘ በመሆኑ የጥላቻ መርዝና ፕሮፓጋንዳ ሲነዙና ሲያራግቡ የነበሩት ሁሉ የሀፍረት ሰማቸውን ተከናነቡ፤ ታሪካዊ ውርደት ተዋረዱ፤ የከተማው ግርግርና የውጭ ኃይሎች ገንዘብ እየተረጨበት ተቀነባብሮ በስልትና በሴራ የተደረገው እንቅስቃሴ ዳግም ላያንሰራራ ተብረክርኮ ወደቀ፡፡ አሸናፊው ሕዝብና መሪው ፓርቲ ኢህአዴግ ሆነ፡፡*

*ይህ ድል ያልተዋጣላቸው ኢትዮጵያዊ ነን የሚሉ ኃይሎች ለዲያስፖራው ጩኸታቸውን በማቅለጥ ደረታቸውን በመድቃት*

*[በመምታት] ከእብደት ባልተናነሰ መልኩ ጌቶቻቸው እግር ሥር ተደፍተው በኢትዮጵያ ላይ የኢኮኖሚ ማዕቀብ እንዲደረግ ያለመታከት ጮኹ፡፡ በድህው ገበሬና በልጆቿ በአጠቃላይም በአራቱም ማዕዘናት በሚገኘው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በ80 ሚሊዮን ወገናቸው ላይ ነበር የዘመቱት፡፡ በሕይወቱ፣ በኑሮው፣ በትምህርቱ፣ በጤናው፣ በልማቱ፣ በዲሞክራሲው ላይ ነበር ሰይፍ የመዘዙት፡፡ ሞትና ጨለማን ነበር የፈረዱበት፡፡*

*የኢትዮጵያን መንግሥት ኃያላን በተባሉት መንግሥታትና ተቋማት አማካኝነት እጁን ሸብለው ሊቆለምሙት አሊያም ተንበርክክልን ሊሉት ደጋግመው ከጅለውታል፡፡ በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ባለቤቶቹ፣ ወሳኞቹ፣ ገዥዎቹ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ብቻ እንጂ የውጭ ኃይሎች አይደሉም፡፡ ከቶውንም ሊሆኑ አይችሉም፡፡ እንዲህ ዓይነት ብሔራዊ ክብርንና ኩራትን አሳልፎ የመስጠት፣ በውስጥ ጉዳያችን በፀጥታና በደህንነት ነጥቦቻችን ከቶውንም በድርድር አንቀርብም፡፡ የሚንበረከክ፣ ክንዱም የሚታጠፍ፣ በድህነታችንም የተነሳ ሎሌነትንና ባርነትን የምንፈቅድ አይደለንም፡፡ የእርዳታ ገንዘባችሁን ይዛችሁ ወደምትሄዱበት መሄድ መብታችሁ ነው የሚለው የፀና የመንግሥት አቋም የውጭ ኃይሎችን አሳፍሮ አንገታቸውን ሊያስደፋቸው በቅቷል፡፡*

*የ1997 ዓ.ምህረቱ ብሔራዊ ምርጫ ዛሬም ትምህርት ያልሆናቸው፣ ዛሬም ዓላማቸውን ለማሳካት በገንዘብ በገዟቸው አንዳንድ ተቃዋሚ ኃይሎችና የግሉ ፕሬስ ተዋናዮች አማካይነት ሊጋልቡ የሚሹ፣ ሁከትና ትርምስ ማየት የሚመኙ፣ የኢትዮጵያን ሚዲያ እንዳሻቸው ሊፈነጩበት በገንዘብ ኃይል አንበርክከው ሊጫወቱበት የወሰኑ ዩ.ኤስ.አይድን የመሳሰሉ ኃይሎች አይናቸውን በጨው ታጥበው እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ፡፡ የዚህ ስውር ዓላማ፣ ግብና ተልዕኮ ግልፅ ነው፡፡ ምርጫ 2002ትን ተከትሎ ትርምስና ሁከት፣ አለመረጋጋት እንዲፈጠር የታቀደ ይመስላል፡፡ ራሱን ችሎ የመንግሥት ዝምታም አስገራሚ ነው፡፡ ዝምታው ግን የግድ ሊያበቃ*

ይገባል፡፡ እንደመንግሥት ማለት ያለበትን ማለት አለበት፡፡ የዶላሩ ምስጢርና ውሻ በበላበት ይጮኻል!

ዩ.ኤስ.ኤይድ ገና 10 ወራት የቀረው "መጪው የ2002 ምርጫ አሳስቦኛል፣ የዲሞክራሲው ማዕቀፍ ጠቧል፣ ተቃዋሚዎች በጠባብ ሜዳ ሊወዳደሩ አይችሉም፣ የፀደቀው መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሕግ አያሰራም፣ "የራሳቸው ም/አምባሳደር ዴቦራ ማላክ ያደነቁትንና የፀደቀውን "የፕሬስ ሕግ ብዙ አያሰራም፣ በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ሕግ ይጣሳል፣ ወዘተ." እያለ በተደጋጋሚ በየኤምባሲው ከተቃዋሚ ኃይሎችና ከአንዳንድ የግሉ ፕሬስ ባለቤቶችና ጋዜጠኞች ጋር ይመክራል፤ ይዘክራል፡፡

ገና የምርጫው ጊዜ ሳይደርስ ምንም ሳይጀመር ከአሁኑ ዩ.ኤስ.ኤይድ ትንቢት እየተናገረ ነው፡፡ ምርጫው ሚዛናዊ አይሆንም እያለ ነው፡፡ ለዚህ ጥናት (survey) አካሂጃለሁ ባይ ነው፡፡ የተለመደው የጥናቱ ምንጮች የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅት መሪዎች፣ የግሉ ፕሬስ ጋዜጣ ባለቤቶችና አንዳንድ ጋዜጠኞች፣ የሲቪክ ማኅበራት መሪዎች ነን የሚሉ ግለሰቦች ናቸው፡፡ በየኤምባሲው ምሣ ወይንም እራት ይጋብዛሉ፡፡ ወይንም በየሆቴሉ ይገናኛሉ፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ጥሩ ተሰርቷል የሚሉት አንድም ነገር የለም፡፡ ልማቱን፣ ትምህርቱን፣ በገሀድ የሚታየውን  የመደራጀትና ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትን እነሱ እያዩም አያዩትም፡፡ ሰፊ የማጥላላት ዘመቻ ያካሂዳሉ፡፡ በየኤምባሲው አሁንም ይመክራሉ፡፡ ያመሻሉ፡፡ ያነጋሉ፡፡ እስቲ ዩ.ኤስ.ኤይድ አሁን ስለኢትዮጵያ ከኢትዮጵያውያን በላይ ምን አስጨነቀው? ከየትኛው ክልል የተገኘስ ኢትዮጵያዊ ነው? እውንስ ለኢትዮጵያ አዝነውና ተቆጭተው ነውን? በቀጥታ ዩ.ኤስ.ኤይድ በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ የኢትዮጵያን የሚዲያ ኃይሎች ተጠቅሞ ጣልቃ መግባት፣ ገንዘብ እንካችሁ ብሎ የግሉን ሚዲያ መጠቀም ለምን ፈለገ? ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲና ሰብአዊ መብት መከበር፣ የሕግ የበላይነት መስፈን፣ የልማቱ መፋጠን፣ የሰላምና መረጋጋት መጐልበት ይበልጥ የሚጥረውና የሚጨነቀው የኢትዮጵያ መንግሥትና የኢትዮጵያ ሕዝብ

ነው? ወይንስ ዩ.ኤስ.ኤይድና አጫፋሪዎቹ ናቸው? ደሞ ያ መከረኛ ምርጫ 2002 ደረሰ፡፡ ስለዚህም የግሉን ሚዲያ አባላት ዩኤስኤይድ በደምበል ዶም ሰብሰቦ "በምርጫው ዙሪያ ሥሩ ፣ተንቀሳቀሱ፣ ጊዜ የለም በገንዘብ ልንረዳችሁ ፈቃደኛ ነን፡፡ ዶላር አለ አስባችሁ ምን ለመስራት እንደምትፈልጉ በጋር ንገሩን " አለ ዩ ኤስ ኤይድ፡፡ "የምርጫው ጉዳይ የራሳችን የውስጥ ጉዳይ ስለሆነ የገንዘብ እርዳታ አያስፈልገንም፡፡ በራሳችን አቅም መስራት እንችላለን፡፡ ለምን ጣልቃ መግባት አስፈለጋችሁ" ተባሉ፡፡ " "የለም በሥልጠናው መስክ እናግዛችሁ ብለን ነው አሉ፡፡"

አሳፋሪ በሆነ ሁኔታ ዩኤስ ኤይድ በመጪው ምርጫ ዙሪያ የገንዘብ እርዳታ ሊያደርግ ነው ተብሎ የተነገራቸው ትላልቆቹም፣ ትናንሾቹም የግል ፕሬሶች ‹‹ ምን እንዳየ ምን ›› አንዴ በጩኸት ተጠራርተው ደምበል ደምን ወረሩት፡፡ አዲስ ነገር ፣ ሪፖርተር፣ አዲስ አድማስ፣ ሰንደቅ፣ አውራምባ፣ ኤፍኤሞች ወዘተ .. በሙሉ ሕጉ የኢትዮጵያን ሚዲያ የውጭ ኃይሎች ፋይናንስ ማድረግ፣ በገንዘብ ማገዝና መርዳት እንደማይችሉ በግልፅ መደንገጉን እንኳን ሺህ ጊዜ በየስብሰባው የሰሙት የግል ፕሬሶች እንዳልሰሙ፣ እንደማያውቁ ሆነው ገንዘብና ጥቅም ፍለጋ ለእኔ ይሰጥ! ለእኔ ይሰጥ! ዓይነት ስግብግብ መራኮት ውስጥ ገብተው ታላቅ ትዝብት አተረፉ፡፡ ለመሆኑ ---- ለመሆኑ የሀገር ክብር፣ የሕዝብ ሕልውና ሰላምና ፀጥታ እንደምን በገንዘብ ይለወጣል? ገንዘብና ትርፍራፊ ሳንቲም ካገኙ ማንንም ከመሸጥ የማይመለሱ፣ በገንዘብም እርስ በእርስ ለእኔ ለእኔ በሚል የሚጣሉ፣ በፕሬሱ ስም የሚንቀሳቀሱ ኃይሎችን ማየት እጅግ የወረደ የዘቀጠ አሳፋሪ ተግባር ነው፡፡ ለሁሉም የ97 ዓ.ም. አይነቱን የጀርዲያ ግልባጭ ‹‹ ብርቱካናማዊውን ›› አብዮት አይነት ፕሬሱን በመጠቀም ለመቀስቀስ ይቻላል ብለው ያሰቡ ወገኖች ሁሉ ከጅልነት ያልዘለለ ሀሳብ ማሰባቸውን ከወዲሁ ቢረዱት የተሻለ ነው፡፡

ዩ ኤስ ኤይድ በቢሊዮንና በትሪሊዮን ኳትሪሊን የሚቆጠር ገንዘብ ሊያንቀሳቅስ፣ ሊረጭ፣ ሊበትን ይችላል፡፡ ለእያንዳንዱ ለሚያወጣት ገንዘብ

*ምላሽ ይጠብቃልና፡፡ ሆኖም ግን የአንዲትን ሉዓላዊት ሀገር ሕግ ረግጠውና ጥሰው እንዳሻቸው እንዲፈነጩ የሚፈቅድ ሕግና መንግሥት እንደሌለ ሊያውቁ ይገባል፡፡*

*መንግሥት በሕግ የበላይነት መከበር፣ በኢትዮጵየ ብሔራዊ ጥቅም ፀጥታና ደህንነት ጉዳይ ከማንም ጋር መደራደርም ሆነ መነጋገር እንደማይቻል ደግሞ ደጋግሞ በተለያዩ በርካታ አጋጣሚዎች አስመስክሯል፡፡*

*ከሁሉ የገረመኝ ነገር ቢኖር የብር አቅማዳቸው ሞልቶ ሊፈስላቸው ባዕዳን ጌቶቻቸው ተንበርክከውና አጎብድደው እጅ ነስተው የሀገራቸውን ክብርና ብሔራዊ ጥቅም ሉዓላዊነት ለእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ኃይሎች አሳልፈው ለመስጠት በብር ጥቅም የታወሩ የግሉ ሚዲያ ባለቤቶችና አንዳንድ ጋዜጠኞችን በገሀድ ማየት መቻሌ ነው፡፡ የኢትዮጵያን ክብርና ነፃነት እንደ ይሁዳ በትንሽ ብር ለመሸጥ ካሰፈሰፉ ኃይሎች እንዴት አይነት የኢትዮጵያዊነት ሥነ ምግባርና ጨዋነት ይጠበቃል? “መሸጥ የለመደ እናቱን ያስማማል” አይደል የሚባለው?*

*ለሁሉም ዩኤስ ኤይድም፣ ሚዲያውን መጠቀም የፈለጉ ኃይሎችም ሁላችሁም እንዳማራችሁ ይቀራል እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ በሰላምና በተሳካ ሁኔታ እንደሚካሄድ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ ዩኤስኤይድም ሆነ ሌሎች እንዲሁም የግሉ ፕሬስ ተዋናዮች ምን እያደረጉና ወዴትስ እየሄዱ እንደሆነ ደጋግመው ሊያስተውሉት ይገባል፡፡ መንግስትም የጉዳዩን ልዩ መልክ በቸልታ ከማለፍ ይልቅ ትኩረት ሊሰጥበት ይገባል፡፡ ዩኤስኤይድ ከዚህ አሳፋሪ የጣልቃ ገብነት ጉዳይ እጁን መሰብሰብ ግድ ይለዋል፡፡ሰላም*